Division of Early Childhood and Title I Programs, and Recovery Funds
የቅድመ ልጅነት እና ታይትል I ፕሮግራሞች ሥራ ክፍል እና የማገገሚያ ፈንዶች

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS, ROCKVILLE, MARYLAND

# ቅድመ-መዋእለ ህፃናት/ ሄድስታርት

## ወላጆች ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች፡-

## 2022–2023 መምሪያ መጽሐፍ (HANDBOOK)

የልጅ ስም፡- ____________________

ለተማሪው(ዋ) ክፍል የፕሪ-ኬ/ሄድስታርት የቤተሰብ
አገልግሎት ሠራተኛ ተመድቧል /ተመድባለች፡- ____________________

የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ የስልክ ቁጥር፡- 240-740-4530







Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

# ቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ማዉጫ
# Pre-K/Head Start Directory

Rocking Horse Road Center
4910 Macon Road, Rockville, MD 2085
240-740-4530
TTY፡- 301-230-5462 ፋክስ፡- 301-230-5401

የቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ተቆጣጣሪ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . Verna Washington-ቨርና ዋሽንግተን

አስተባባሪ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ጄሲካ ብለሲክ Jessica Blasic

የሂሳብ ሰራተኛ ግሎሪያ ዳያዝ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . Gloria Diaz
የትምህርት ቤት ሬጅስትራር ተስፋዬ ሙሉነህ Tesfaye Muluneh
አነማሪ ዎከር AnneMarie Walker

የመረጃዎች(ዳታ) ሲስተም ኦፐሬተርግዩንጌ ኪም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .Gyungae Kim
ኤልሳ ሪኦስ Elsa Rios

አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጸሐፊ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ካሪይን ስተይን Caryn Stein
ጃኔት ዜፒዳ እስኮባር Jeannette Zepeda Escobar

# የልጆች እድገት እና ትምህርት ሠራተኞች-
# Child Development and Education Staff 240-740-4530

የትምህርት ስፔሻሊስትመሊሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ክሪፍ Melisha Creef
ሎዊስ ቶሊን Louise Tolin
ጂጂ ኦልድስ Jiji Olds
ዴይድራ ፉለር Deirdra Fuller
ኬሊ ባሬ Kelly Barre

የፕሮግራም ረዳት አስተማሪዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ሶናሊ ሞዛ Sonali Motha

ሱዛን ዶውሊንግ Susan Dowling
የፕሪ ኬ (Pre-K) ከዋናው ቤሮ አስተማሪዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ሻልኒ ኮማል Shalini Komal
ሾና ዌቨር Shona Weaver

ሳይኮሎጂስቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ማሪሳ ሴንሰ-Marissa Senese
ጁሊ ሼይልድስ Julie Shields
ሳራ ማኪን Sara McKeen
ቪክቶሪያ ዊሊንግሃም Victoria Willingham
ገብሬላ ኢስተቬዝ Gabriella Estevez

የንግግር-የስነልሣን ባለሙያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ጆ አን ሮቢንሰን Joe Ann Robinson
ላይን ቴዎማን Lynne Teoman

## የጤና አገልግሎት ሰራተኞች . . . . . . . . . . . .240-777-1553

የጤና አገልግሎት ማናጀርቤካ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ኡርጌሳ Beka Urgessa

የጥርስ ሀኪምሌስሊ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ኮንስበርግ Lesley Konigsburg
ቴረሳ ሱዳክ Teresa Soodak
ሲንዲ ዛንደር Cindy Xander

ነርሶችሚና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . አሊባዲ Mina Aliabadi
ፓምላ ጋምቦን Pamela Gambon
ረኔ ማክኔቪን Renee McNevin
ኪምበርሊ ሙሃመድ Kimberly Muhammed
ኖምቩዮ ኩቤካ Nomvuyo Qubeka
ሲሞኔ ሮበርትስ Simone Roberts
ፓትሪሽያ ዊንተርስ Patricia Winters

የጤና ረዳቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ኖርማ ዴቪስ Norma Davis
ተሬሳ ሆክ Teresa Hock
ቼሪል ፓይል Cheryl Pyle

የብቃት ምልመላ ስፔሻሊስትዎንድ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ወርቃለማሁ Wond Workalemahu

## የወላጅ፣ ቤተሰብ፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ሰራተኛ. . . .240-740-4530

የማህበራዊ አገልግሎቶች ልዩ ባለሙያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ሊዛ ኮንሎን Lisa Conlon

የማህበራዊ ሰራተኞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . አኔት ሀሪስ Annette Harris
ቫለሪ ቻስትሪሎ Valeria Castrillo
ረኔ ፎስተር Renée Foster
ቴሪ ቶምሰን Terry Fisher Thompson
ተርሻ ፖወል Traci Powell

የወላጅ፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ
ተሳትፎ/የበጎ ፈቃደኝነት ባለሙያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ጆሴ ሮቤርቶ ፍሎሬስ Jose Roberto Flores

### የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኞች

ፒላር አባርካ Pilar Abarca
ማራል አብካርያን Maral Abkarian
ኪይራ ኦስቲን Kiara Austin
ጃዝሚ ቤጋዞ Jazmina Begazo
ኤልሲ ቦኒላ Elsi Bonilla
ካቸር ካርተር Cachet Carter
ጆስልይን ቺካ ቫልዴዝ Joselyn Chica Valdez
ለስቲን ኮልበርት Lestine Colbert
ሳንድራ ክሩዝ Sandra Cruz
ቴሬሳ ዴልጋዲሎ Teresa Delgadillo
ዳማራ ዶክሪ Damara Dockery
ሚሼል ዶቭ Michelle Dove
ሬንያ ኤስካሚላ Reyna Escamilla
ሮዛ ኤስኮባር Rosa Escobar
ኤስፔራንዛ ፍሎሬስ Esperanza Flores
ዴቦራ ጋርሲያ Deborah Garcia
ሶንያ ግራናዶስ ዴ ቫልዴዝ Sonia Granados de Valdez
ቪያንካ ሃርዲይ Vianka Hardy
ቴሪ ሀሪስ Terri Harris
ሶራንገል ፐራልታ ሄራራ Sorangel Peralta Herrera
ሳሚራ ሁሴን Samira Hussein
ቪኪ ጆንሰን Vicki Johnson
ኑሃካላፍ Nuha Khalaf
ፓቲ ማሮኩይን Patty Marroquin
ሊይዳ ማርቲነዝ Leida Martinez
ሩት ሜንንጀር Ruth Meininger
አማቢላ ሬይስ Amabilia Reyes
ዳኒዬላ ሮድሪጌ Daniela Rodriguez
ኬቪን ሺም Kevin Shim
ተሪሻ ስተቨንስ Traci Stevens
ረኒ ተነያክ Renee Teneyck
ሴሲያ ቬንቱራ Cesiah Ventura

# ማውጫ


የፕሮግራም ዲዛይን እና አስተዳደር/ማኔጅመንት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ተማሪዎችን ለስኬት ማዘጋጀት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
የፖሊሲ ካውንስል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
የፖሊሲ ካውንስል ኃላፊዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
የፖሊሲ ካውንስል ሀላፊነቶች/ሥልጣን. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
የልጅ እድገት እና ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
አይነተኛ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ቀን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
ስለ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት እና ሄድስታርት ፕሮግራሞች/MCPS Pre-K እና Head Start Programs መታወቅ ያለባቸዉ ሌሎች ነገሮች . . . . . . . . . . . . 2
ምግቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
የመስክ ጉዞዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የግል ደህንነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ንግግር/ቋንቋ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ልብስ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
መከታተል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የቤት ጉብኝቶችና የወላጅ-መምህር ስብሰባዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የአስቸኳይ ጊዜ መዘጋት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
በቅድሚያ የሚለቀቁበት ቀናት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ልጆች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የእንግሊዝኛ ተማሪዎች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የጤና አገልግሎቶች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
ወላጅ፣ ቤተሰብ፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
በጎ-ፈቃደኞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
መጓጓዣ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የወላጅ/ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
ሌላ መረጃ/ኢንፎርሜሽን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
ተቀዳሚ ሄድ ስታርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
የልጅ እንክብካቤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ሙከራ ፕሮግራም (Pre-K+). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
በቅድመ መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ የሚዉሉ ቃላት . . . . . . . . . . 8
2022–2023 ካላንደር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

## የፕሮግራም ዲዛይን እና አስተዳደር/ ማኔጅመንት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር በጋራ እና ከማህበረሰቡ ባለድርሻ አካላት፣ የካውንቲውን የመንግስት አስተዳደር፣ እና የስቴት እና የአካባቢ ኤጀንሲዎችን ጨምሮ በትብብር፣ ለእያንዳንዱ ልጅ በከፍተኛ ጥራት የልጅነት እድሜ ተሞክሮ፣ ጠንካራ መሠረት የሚፈጥር ቁልፍ የሆነ ትምህርትና እድገት፣ በእያንዳንዱ ተከታታይ የክፍል ደረጃ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ወደ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ የአካደሚና የግል ህይወት ስኬት እንዲኖራቸዉ የሚያስችል የቅድመ መዋዕለ ህጻናት እና ሄድስታርት ፕሮግራሞችን ያቀርባል/ይሰጣል። በቅርቡ የተሻሻለው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IEA፣ የለጋ ልጅነት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማእቀፍ ፣

የካውንቲውን፣ የስቴት፣ እና የፌደራል ሪሶርሶችን ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም፣ መሠረታዊ የአገልግሎት ፍላጎት ያላቸዉን ህፃናት ለመለየት እና በእያንዳንዱ የልጆች እድገት ደረጃ ከቤት፣ ከሕጻናት እንክብካቤ ወይም ከቅድመ ት/ቤት ወደ ቅድመ መዋዕለ ህፃናት፣ እንደየ አግባቡ፣ እና ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላኛው በሚያሳዩት የእድገት ደረጃ፣ የተማሪን እድገት፣ ሽግግር፣ ምደባ እና የፕሮግራም ዘላቂነትን ለማመቻቸት፣ ትናንሽ ልጆች እና ቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልጓቸው አስፈላጊ አገልግሎቶችን ስለመስጠት የቦርዱ ቁርጠኝነት በዝርዝር ቀርቧል።

ቦርዱ በመጀመሪያዎቹ አመታት ከልደት እስከ 5 አመት ህጻናትን ለመደገፍ በመላ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ካሉ የህዝብ እና የግል ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የቅድመ እንክብካቤ እና ትምህርት ተነሳሽነት የድርጊት መርሃ ግብር እና የሜሪላንድ ብሉፕሪንት ላይ በተገለጸው መሰረት ለወደፊት የት/ቤት ስኬት ያዘጋጃቸዋል። MCPS ከልደት እስከ 8 አመት ለሆኑ ህጻናት የተለያዩ የማጣሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን በቤት እና በትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እና በሌሎች ማእከላዊ ፕሮግራሞች ያቀርባል። በስፋት አገልግሎቶች የሚሰጡት ልጆች ባላቸው የተለያየ ፍላጎት መሠረት በተለያየ ደረጃ ስለ ንግግር/ስነ-ቋንቋ፣ የመስማት/ማዳመጥ፣ የማየት፣ የሰውነት መገጣጠሚያ/orthopedic እና የእድገት ዘገምተኝነትን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተመሠረተ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

በ MCPS፣ የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት/ሄድስታርት ሱፐርቫይዘር፤ የግራንት መስፈርቶችን አፈጻጸም በሚመለከት ከፖሊሲ ካውንስል፣ ከማህበረሰብ አክሽን ኤጀንሲ፣ ከሪጅን III ጽ/ቤት፣ እና ከ MCPS ጋር ያስተባብራል/ታስተባብራለች። ይህ ቡድን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ቤተሰቦች እና የቅድመ ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን ፍላጎቶች ለማሟላት አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር ግንኙነትን ያዳብራል እና ያሳድጋል። ሱፐርቫይዘሩ(ሯ) የቅድመ መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ወላጆችን ፍላጎት ለማገዝ፣ የፕሮግራሙን ግብ፣ አላማ፣ እና ውጤቶችን ይገመግማል/ትገመግማለች እናም ያሻሽላል/ታሻሽላለች።

## ተማሪዎችን ለስኬታማነት ማዘጋጀት

የ MCPS ቅድመ መዋዕለ ህጻናት /ሄድስታርት ክፍል ለህጻናት የትምህርት ዝግጁነት ድጋፍ የሚሆኑ ሰፋ ያሉ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ለትምህርት ቤት ዝግጁነት ማለት ልጆች በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስችላቸዉ ክህሎቶች፣ ችሎታዎች እና ዝንባሌ ይኖሯቸዋል ማለት ነው። ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆች የመጀመሪያ እና በጣም አስፈላጊ መምህራን ናቸዉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ የፕሮግራሙ ስራ ባልደረቦች፣ እና ሌሎች የቤተሰብ እና የማህበረሰብ አባላት ሁሉም ልጆችን ለትምህርት ቤት በማዘጋጀት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።

## የፖሊሲ ካውንስል

እያንዳንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለቅድመ መዋእለ ህጻናት/ሄድስታርት የፖሊሲ ካውንስል አባልነት የወላጅ/የሞግዚት ተወካይ ይመርጣል። ተወካዮቹ ሌሎች ወላጆች/አሳዳጊዎችን በማሳወቅ እና የሥራ እንቅስቃሴ እቅድ በማውጣት ይሠራሉ። አዳዲስ ተተኪ ኃላፊዎች በዲሴምበር ተመርጠው ጃንዩወሪ ላይ ሥራቸውን ይረከባሉ።

የፖሊሲ ካውንስል ወላጅ/አሳዳጊ ልዑካን በየወሩ በ6፡00 ፒ.ኤም፣ በዙም ይገናኛሉ። ስብሰባዎች በሴፕቴምበር መጨረሻ ወይም በኦክቶበር መጀመርያ ላይ መግለጫ በመስጠት/የስልጠና ክፍልጊዜዎች ይጀምራሉ። የበጀት ሰብሰባ የሚካሄደው በኦክቶበሩ ስብሰባ ነው፣ ከዚያ በኋላ መደበኛ የወር ስብሰባዎች በየወሩ ሶስተኛ ሀሙስ ይካሄዳሉ። ተጨማሪ የወላጅ ተሳትፎን ለማመቻቸት ስብሰባዎች በዙም ይካሄዳሉ። የስብሰባ መግቢያ መለያ እና የይለፍ ቃል (meeting ID and password) የመሣሰሉት የስብሰባ መረጃዎች ለወላጆች በመግለጫ ወቅት ይሰጣሉ።

## የፖሊሲ ካውንስል ኃላፊዎች

የፖሊሲ ካውንስል ተመራጭ ኃላፊዎች የየወሩን ስብሰባዎች አጀንዳ አዘጋጅተው ለጠቅላላ አባላት ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ።

ሊቀመንበር
ምክትል ሊቀመንበሮች (2)
ገንዘብ ያዥ
የሪከርድ ጸሐፊ
የህዝብ ግንኙነት ጸሐፊ
የህብረተሰብ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ተወካዮች (2)
የሜሪላንድ ስቴት ሄድስታርት ተወካዮች (2)
የእርስዎ ማዕከል የፖሊሲ ካውንስል ተወካይ

____________________________________

የስልክ ቁጥር፡- __________________________

የእርስዎ ማእከል የፖሊሲ ካውንስል ተለዋጭ አባል፡-

____________________________________

የስልክ ቁጥር፡- __________________________

የፖሊሲ ካውንስል ተወካዮች ከኪሳቸው ለሚያወጡት ወጪ ከ "Parent Activity Fund" ይከፈላቸዋል። ካውንስሉ በየአምቱ የበጀት ማስተካከያ ከሠራ በኋላ ባወጡት ወጪ ምትክ የሚከፈለውን ገንዘብ መጠን ይወስናል። ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች በፖሊሲ ካውንስል ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ እና እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ቢሆንም፣ ድምፅ መስጠት የሚችሉት ተመራጭ ተወካዮች ብቻ ናቸው።

የፖሊሲ ምክር ቤት ከቅድመ-መዋዕለ ሕፃናት/ሄድስታርት አገልግሎት ጋር የተያያዙ፣ እንደ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ ትምህርት፣ የአካል ጉዳት ላለባቸው የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ እና ጤና የመሳሰሉ ተግባራትን የሚያቅድ እና የሚተገብር ንዑስ ኮሚቴዎች አሉት። ሌሎች ንኡስ ኮሚቴዎች ከፕሮግራም አመራር ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

## የፖሊሲ ካውንስል ኃላፊነቶች

- ለወላጅ እንቅስቃሴ አስፈላጊ በጀት ያዘጋጃል
- በፕሮግራም ግምገማዎች ይሳተፋል
- የልጅና ቤተሰብ ደንብ/ድንጋጌ አፈፃጸምን ይደግፋል።
- ከተጋባዥ ተናጋሪዎች ጋር ፕሮግራሞች ያደራጃል።
- የቤተሰብ ሽርሽሮችና ክውነቶችን ያስተናግዳል
- የፕሮግራም በጀት እና የፕሮጀክት ሀሳብ ዝግጅቶችን ያግዛል
- የአገልግሎት ሰጪ ኮሚቴዎችን ያገለግላል
- የልጆች ምልመላ እቅዶችን ያዘጋጃል

## የልጅ አእምሮ መዳበርና ትምህርት

ልጆች በቅድመ-መዋዕል ሕፃናት/ሄድስታርት ፕሮግራም ዉስጥ በጣም ይጫወታሉ። ጨዋታ የትናንሽ ልጆች ስራ ነው፤ ይህ ነው የመማርያ ዘዴአቸው። ልጆች በመዋዕለ ሕጻናት ውስጥ ለስኬት ሲዘጋጁ፣ የሚከተሉትን ያከናውናሉ ፡-

- ትናንሽና ትላልቅ ጡንቻዎችን ያዳብራሉ
- ተረቶችን ያዳምጣሉ፥ መፃህፍትንም ይመለከታሉ።
- ቀለም መቀባት፣ ስእል መስራት፣ እና መፍጠር
- በሳይንስ ቁሳቁሶች ዳሰሳ ማድረግ
- ትያትር መጫወት እና ታሪኮችንና መዝሙሮችን/ዘፈኖችን መጫወት
- ማዳመጥ፣ መደነስ፣ መዝፈን/መዘመር፣ እና ሙዚቃ መስራት
- እንቆቅልሾችን መሥራት የተለያየ አይነት ጨዋታዎችን መጫወት
- ስሞችን፣ ቀለሞችን፣ እና ቁጥሮችን መለየት
- መጋራትንና መተባበርን መማር

የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ክፍል የልጆችን ስሜታዊ፣ የአእምሮ/የአስተሳሰብ፣ ማህበራዊ፣ እና አካላዊ እድገትን ያበለጽጋል።

## ልዩ የቅድመ መዋለ ህጻናት/ሄድስታርት የመጀመሪያ ቀን

- መክፈቻ፡- እንኳን ደህና መጣችሁ መዝሙር/ዘፈን
  የአየር ሁኔታ
  የቀን መቁጠሪያ
- መላ የማንበብና የመፃፍ ብሎክ፡-
  መፃህፍትና ታሪኮች
  መዝሙሮች/ዘፈኖችና የድምፅ፣
  የእንቅስቃሴ ቅኝቶች
  ሆሄያት Alphabet
  አማርኛ Amharic
- ትንሽ የሊተርሲ ቡድን ብሎክ፡-
  የንግግር የቃል ቋንቋ
  ስለፊደላት ፅንሰሀሳቦች
  የንግግር ድምጽ አወጣጥ
  ዘይቤዎች
  የፊደል እውቀት
- የማእከል ጊዜ፡- የድራማ ጨዋታ
  የማንበብና የመፃፍ ማእከሎች
  በድጋፍ ፍንጭ የተመቻቹ—
  ማእዘኖች
  ሂሳብ/የአሠራር ዘዴዎች
  የሳይንስ ፕሮጀክቶች
  ማብሰል
- የሂሳብ ብሎክ፡- የቁጥር ፅንሰሀሳቦች
  በአይነት መለያየትና ተመሣሣይ
  ንድፎች/ቅርፀቶች
- ከቤት ውጭ ጨዋታ፡- የአካላዊ እንቅስቃሴ ሞተር
  ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች
- ምሳ

## ስለ MCPS ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ሄድስታርት ፕሮግራሞችን በተመለከተ ሌሎች መታወቅ ያለባቸው ነገሮች

### ምግቦች

የሄድስታርት ልጆች በየእለቱ የቤተሰብ ወጪ የሌለበት የት/ቤት ምሳ ያገኛሉ። የቁርስ ፕሮግራሞች ያሏቸው ት/ቤቶችም፣ ትምህርት አስቀድሞ የሚጀመር ከሆነ ለሄድስታርት ልጆች ቁርስ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

በክፍል ውስጥ የማብሰል እና የመቅመስ እንቅስቃሴዎች ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ልጆች አዳዲስ እና ጥሩ የተመጣጠኑ ምግቦችን ጣእም የመቅመስ ሌሎች ልምዶችን ይሰጣል። ወላጆች/ሞግዚቶች ከልጆች ጋር ለማቀድ እና አብረው ምግብ እንዲያበስሉ ለመርዳት ተጋብዘዋል።

እንደ በጎ ፈቃደኛ ወይም ጎብኚ፣ የሄድስታርት ወላጆች/ሞግዚቶች ወደ ት/ቤት ሲመጡ በክፍል ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ምሳ እንዲጋሩ ይጋበዛሉ።

### የመስክ ጉዞዎች

የመስክ ጉዞዎች የልጆችን ባህላዊ ተሞክሮዎች ያዳብራሉ፣ አድማሳቸውን ያሰፋሉ፣ እናም የራሳቸውን አካባቢ ግንዛቤ ይጨምራሉ።

### የግል ደህንነት

የደህንነት ሥርዓተ ትምህርት አካል እንደመሆኑ፣ ልጆች ለአዋቂዎች "አልፈልግም/አይሆንም" የማለት ፍቃድ መስጠትን ጨምሮ፣ የግል የደህንነት ቴክኒኮችን እንዲማሩ፣ እና ልጆች ደህንነታቸዉ ስጋት ላይ መሆኑ ሲሰማቸው ለሚያምኑት አዋቂ እንዲናገሩ በማበረታታት ይማራሉ። ሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች የማጎሳቆል እና የቸልተኝነት ሁኔታዎችን ሪፖርት እንዲያደርጉ የሜሪላንድ ስቴት ሕግ እንደሚጠይቅ ወላጆች/ሞግዚቶች ማወቅ አለባቸው።

### ንግግር/ቋንቋ

የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት (Pre-K /Head Start Unit) ክፍል የንግግር/የስነ ልሳን ስፔሻሊስቶች/ፓቶሎጅስቶች እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎች/ሳይኮሎጅስቶች የሚሰጡት የለጋ-ልጅነት/early-childhood ትምህርት ልዩ ስልጠና አላቸው፤ ለልጆች እና ለቤተሰቦች አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

### ልብስ

ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት የጨዋታ ልብሶች ተገቢ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ልጆች የሆኑ ነገሮችን ያፈሳሉ፣ ይረጥባሉ ወይም በልብሳቸዉ ላይ የሆነ አደጋ ሊፈጠር ይችላል። ንጹህ ልብሶች  አስፈላጊ ሲሆን እንዲቀርብ ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪ ስም የተጻፈበት/የተለጠፈበት ቅያሪ ልብሶችን እንዲልኩ ይጠየቃሉ። የዝናብ ልብሶች፣ ቦት ጫማዎች፣ የእጅ ጓንቶች፣ እና ሌላ ዓይነት ልብሶችም ከሌሎች ጋር መደባለቅን ለመከላከል የልጅዎ ስም ለምልክት እንዲኖርባቸዉ ያስፈልጋል።

### ክፍል ውስጥ መገኘት

ለተማሪዎች በየቀኑ ት/ቤት መከታተል እና በሰዓቱ መድረስ አስፈላጊ ነዉ። ለእያንዳንዱ/ዷ ልጅ ከቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ተሞክሮ የበለጠ ጥቅም ለማግኘት አዘውትሮ መገኘት/መከታተል አስፈላጊ ነው። ዘወትር ወደ ት/ቤት መሄድ እና በሰዓት መገኘት ልጅዎ ስለ ትም/ቤት ስለሚያዳብረው/ስለምታዳብረው አስተሳሰብ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ስለ ት/ቤት የሚገነባ አወንታዊ አቋም እና የተሟላ ክትትል በመጪዎቹ አመታት ይክሳል።

ልጆች በሰዓቱ ት/ቤት ሲደርሱ፣ በቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ዉስጥ የተሻለ የትምህርት እና ማህበራዊ ተሞክሮ ይኖራቸዋል። ልጅዎ ከታመመ/ች፣ ት/ቤት ይደዉሉ እና ለመምህር መልዕክት ይተው። ልጅዎ መመለስ ሲችል/ስትችል፣ የቀረ/ችበትን ምክንያት በመግለጽ ማስታወሻ በልጅዎ ይላኩ። እባክዎት ስለ ማንኛውም የልጅዎ ህመም ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ምንጊዜም የልጅዎ መምህር ወይም የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ እንዲያውቁ አድርጉ። ልጅዎ በወር ውስጥ 3 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከቀረ/ች፣ ቀኖቹ በተከታታይ ቢሆንም/ባይሆኑም፣ በቤተሰብ የአገልግሎት ሰራተኛ ክትትል ይደረጋል። የእርስዎ ልጅ 10 ወይም የሚበልጥ ተከታታይ ቀኖች ትምህርት ላይ ካልተገኘ/ች፣ እና በህመም ምክንያት መቅረት ካልሆነ ልጅዎ ከፕሮግራሙ ይወጣል/ትወጣለች።

### የቤት ጉብኝቶች እና የወላጅ-መምህር ስብሰባዎች

በ ሄድስታርት እና ቅድመ መዋእለ ህጻናት ለሚገኙ ተማሪዎች፣ የእርስዎ ልጅ መምህር/ት እና ረዳት አሥተማሪ ሴፕቴምበር ላይ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት ቤትዎን ይጎበኛሉ። ለ "Pre-K" ተማሪዎች፣ የልጅዎ አስተማሪ እና ረዳት አስተማሪ በትምህርት ቤት ወይም በቤት የቤተሰብ ጉብኝት ያደርጋሉ። የ ሄድስታርት-"Head Start እና ቅድመ መዋእለ ህጻናት-Pre-K Pilot (Pre-K+)" ቤተሰቦች ፌብሩወሪ ላይ ሌላ የቤት ጉብኝት ይደረጋል። በተጨማሪ፣ ሁለት ስብሰባዎች ይኖሯቸዋል—አንድ በኖቬምበር እና አንድ በጁን። ወላጆች/አሳዳጊዎች በሌላ ጊዜ ከልጃቸዉ መምህር ጋር ለመገናኘት ለት/ቤቱ ደዉለዉ ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ።

የቤት ውስጥ ጉብኝቶች እና ከልጅዎ መምህር ጋር ስብሰባዎች ስለ ልጆችዎ መረጃ ለመለዋወጥ ጥሩ እድል ይሰጣሉ። ይህ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት በቤት እና በት/ቤት መካከል ወደ ዘለቄታዊ አጋርነት ያመራል። እንደዚህ አይነቶቹ ትብብሮች ከዳበሩ፣ የእርስዎ ልጅ  ለሚያስደስትና ለስኬታማ ተሞክሮ የበለጠ እድል ይኖረዋል/ይኖራታል።

### በድንገተኛ ሁኔታ የሚዘጉ ቀኖች/ Emergency Closings

በመጥፎ የአየር ሁኔታ ወይም ሌሎች ድንገተኛ ሁኔታዎች ካሉ፣ የ MCPS ትምህርት ቤቶች ቀኑን ሙሉ ሊዘጉ ወይም ትምህርት ቤት የሚከፈትበት ጊዜ ለሁለት ሰዓታት ሊዘገይ ይችላል።

- የትምህርት መጀመርያ በሁለት ሰአት እንዲዘገይ ከተደረገ፣ የጠዋት ቅድመ መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ክፍሎች አይኖሩም። የከሰአት በኋላ ትምህርቶች እንደተለመደው ይካሄዳሉ።
- በመጥፎ የአየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤቶች ቀድመዉ ከተዘጉ፣ የጠዋት ቅድመ መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ልጆች ቀደም ብለዉ ወደ ቤት የሚመለሱ ሲሆን፤ የከሰዓት በኋላ ቅድመ መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ክፍሎች አይኖሩም።
- ት/ቤት ሙሉውን ቀን ከተዘጋ፣ ወይም ት/ቤት አስቀድሞ ከተዘጋ፣ ሁሉም የምሽት እንቅስቃሴዎች ወድያውኑ ይሰረዛሉ፣ እናም የፖሊሲ ካውንስል ስብሰባ ወይም የጎልማሶች ትምህርት አይኖርም።

የትምህርት ቤት መዘጋት መረጃ በአካባቢ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ በ MCPS የኬብል መስመሮች (Channel 34 on Comcast, 36 በ Verizon ላይ እና በ RCN ኬብል 89 ላይ)፣ እና በ MCPS ድረገጽ (www.montgomeryschoolsmd.org) ይሰራጫል። እንዲሁም መረጃ በ MCPS ቲዊተር አካዉንት (twitter.com/MCPS)፤ የ MCPS ፌስቡክ አካዉንት(www.facebook.com/mcpsmd/) እንደሚያገኙ፤ እና እንዲሁም MCPS በ Connect-ED (ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች በተሰጠ የድንገተኛ ጊዜ ቁጥሮች እና የኢሜል አድራሻዎችን የሚጠቀም የመደወያ እና የኢ-ሜል መላኪያ ስርዓት) መልዕክት ይተላለፋል። እንዲሁም፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የማንቂያ ሲስተም የጽሁፍ/ቴክስት እና የኢሜል መልእክቶችን ለማግኘት መመዝገብ ይችላሉ (www.montgomeryschoolsmd.org/emergency/alertmcps.aspx)።

### በድቅድሚያ የሚለቀቁባቸው ቀኖች

ቀደም ብሎ በሚለቀቁባቸው ቀናት ቅድመ-መዋለ-ህፃናት/ሄድስታርት ክፍሎች በተለየ ሁኔታ መርሀግብር ተይዞላቸዋል። የልጅዎ መምህር የመለቀቂያ ሰአቶችን ያስታውቋችኋል። በተጨማሪ፣ እነዚህ አስቀድሞ የሚለቀቁባቸው ቀኖች ከመድረሳቸው በፊት ማሳሰቢያ ይላካል።

ሴፕቴምበር 14
ሴፕቴምበር 30
ማርች 3
ማርች 15
ጁን 15 (ለተማሪዎች የመጨረሻው ቀን)

### የአካል ጉዳተኛ/ስንክልና ያላቸዉ ልጆች

ሄድስታርት በፌደራል በጀት የሚካሄድ ፕሮግራም ነዉ። የአካል ጉዳተኛ/ስንክልና ያላቸዉ ልጆች ለፕሮግራሙ ከሚመዘገቡት ከመቶ እጅ አስሩን (10 ፐርሰንት) እንዲይዙ ያዛል። አካል ጉዳተኛ ልጆች ቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድ ስታርት ክፍሎችን በማደግ ላይ ካሉ እኩዮቻቸው (የማካተት ሞዴል) ጋር ይማራሉ፣ ሁሉም የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት/ሄድ ስታርት ልጆች የሚያገኙትን ሁሉንም አገልግሎቶች እና ልዩ እንክብካቤዎችን ያገኛሉ። የመማሪያ ክፍል እንቅስቃሴዎች እና ተሞክሮች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን በሚያሳትፍ መልኩ እንዲስተካከሉ ይደረጋል።

ሁሉም ልጆች አንድ ላይ የሚማሩበት እና የሚያድጉበት ጊዜ እንደመሆኑ መጠን፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ አስተማሪዎች፣ እና ልጆች በአካታች ሞዴል/inclusion model ይደሰታሉ። ስለ ልጃቸው እድገት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች የሥራ ባልደረቦች መልስ ይሰጣሉ። በተጨማሪም፣ የሥራ ባልደረቦች ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ልጃቸዉ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው በተለየ አካባቢ የሚያግዝ/የሚረዳ በቤት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባሮችን ይሰጣሉ። ልጆች በተለያዩ የእድገት ዘርፎች የማጣሪያ ምርመራ ይደረግላቸዋል (ትምህርታዊ፣ የንግግር/የቋንቋ፣ ዕይታ፣ ጥርስ እና መስማት።) በማጣሪያ ምርመራው መሰረት፣ የትምህርት ስንክልና ከተጠረጠረ፣ የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን(ለምሳሌ፣ መምህራን፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የት/ቤት ስነ-ልቦና ባለሙያ፣ ልዩ ትምህርት አስተማሪ፣ የስነ-ልሣን ንግግር ባለሙያ (ፓቶሎጂስት)፣ ነርስ፣ ወዘተ) ተጨማሪ ምዘናዎች/ምርመራዎች እንደሚያስፈልጉ ለመወሰን ይሰበሰባሉ። ሌሎች ተጨማሪ ምዘናዎች/ምርመራዎች እንዲደረጉ ከተመከረ/ከተወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ ለምርመራዎቹ የወላጅ/የአሳዳጊ ስምምነት ማግኘት አለበት።

ምርመራዎቹ እና ግምገማዎቹ ከተጠናቀቁ በኋላ፣ የ IEP ቡድን ምን አይነት የትምህርት ስንክልና እንደሆነ መወሰን አለበት፣ ከሆነም የትኛው የፌዴራል የትምህርት ስንክልና ኮዶች የተማሪዉን/ዋን ስንክልና እንደሚገልፅ ይለያል። የትምህርት ስንክልና መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ፣ እና የ IEP ቡድን ስንክልናዉ በተማሪው/ዋ መማር ላይ ተፅእኖ ማሳደሩን ከወሰነ፣ ተገቢ ግቦች እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ላይ ዉይይት ይደረጋል ።

ተፈላጊ አገልግሎቶች በቅድመ-መዋዕል ህጻናት/ሄድስታርት ፕሮግራም ወይም በሌላ የ MCPS ፕሮግራሞች በኩል ሊሰጡ ይችላሉ። ልጅዎ በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት/ (Pre-K / Head Start) የመማሪያ ክፍል ለቀርብ ከሚችል የበለጠ የልዩ ትምህርት አገልግሎት ወይም በ MCPS ከሚቀርቡ አገልግሎቶች የተለየ የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነ፣ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ሰራተኛ የተወሰነዉን/ የተመከረዉን አገልግሎቶች ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዴት/ከየት እንደሚያገኙ ሊረዷቸው ይችላሉ።

በልጅዎ እድገት ውስጥ ሊያዩዋቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- ንግግርና ቋንቋ፡- ልጅዎ በግልጽ መናገር እና ቋንቋን መረዳት ይችላል/ትችላለች?
- እውቅና/Cognitive፡- ልጅዎ ተመሳሳይ ዕድሜ ካላቸው ከሌሎች ልጆች ጋር እኩል በሆነ መልኩ እየተማረ እና እያደገ ነው ወይ?
- ግርድፍና ረቂቅ እንቅስቃሴ/Gross and Fine Motor፡ - ልጅዎ "ገልጃጃ" ነው/ናት ወይም ልጅዎ በእጁ/ጇ በመጠቀም በብሎክ ለመጫወት ወይም በወረቀት ላይ ለመጫር ችግር አለበት/ባት ወይ?
- ማህበራዊ/ስሜታዊ ልጅዎ ከሌሎች ልጆችና ጎልማሶች ጋር ይስማማልን/ትስማማለችን?
- ማሳሰብያ፡- ልጅዎ በዕድሜ እኩያ ከሆኑ ከሌሎች ልጆች ይልቅ በእርጋታ ቁጭ የማለት ወይም ትኩረት የመስጠት ችግር አለበት/ባት ወይ?
- ማዳመጥ/መስማት ወይም ማየት፡- ልጅዎ መጽሐፍትን ወይም ቴሌቪዥን ሲመለከት/ስትመለከት ዓይኑን/ኗን በከፊል ይጨፍናል/ትጨፍናለች ወይ? ልጅዎ በአካባቢው/ዋ ለሚፈጠር ድምጽ በአግባቡ ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች ወይ ?

የልጅዎን እድገት በተመለከተ ስጋት ካለዎት፣ ለአስተማሪዎ ያሳውቁ፣ ወይም ለቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ክፍል በ240-740-4530ይደውሉ።

### የእንግሊዘኛ ተማሪዎች

በፌዴራል እና በስቴት መስፈርቶች መሠረት፣ ሁሉም የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ወላጆች/አሳዳጊዎች በምዝገባ ወቅት የሚሪላንድ በቤት የሚጠቀሙበትን ቋንቋ የዳሰሳ ጥናት ቅጽ ይሞላሉ። ልጅዎ በቤት ውስጥ ስለሚናገረው/ስለምትናገረዉ ቋንቋ መረጃ ይሰጣል።

## የጤና አገልግሎቶች

ለቅድመ-መዋለ ሕጻናት/ሄድስታርት እንደ ቅድመ ሁኔታ፣ ሁሉም ተማሪዎች አካላዊ ምርመራ፣ የስቴትና የፌድራል ተፈላጊ ክትባቶች፣ የደም ምርመራና የጥርስ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ልጅዎ አካላዊ ምርመራ እና ክትባቶች ለመቀበል የጤና እንክብካቤ ምንጭ ከሌለው/ከሌላት፣ እነዚህን አገልግሎት ማግኘት እንዲ(ድት)ችል እባክዎ የልጅዎ አስተማሪ፣ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ፣ ወይም የት/ቤቱ ነርስ እንዲያውቁ ያድርጉ። ለስቴት እና ለአካባቢ የጤና እና የአመጋገብ ፕሮግራሞች፣ በሚከተሉት ቦታዎች በሚገኙ የብቁነት እና የድጋፍ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (OESS) ለቤተሰብዎ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

12900 Middlebrook Road
Germantown, MD 20874 . . . . .240-777-3591

1401 Rockville Pike
Rockville, MD 20852 . . . . . . .240-777-3120

8630 Fenton Street
Silver Spring, MD 20910 . . . . .240-777-3066

4910 Macon Road
Rockville, MD 20852 . . . . . . .240-740-4430

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ጥበቃ ማዕከሎች እና MCPS Health Services Center at Rocking Horse Road Center (4910 Macon Road, Rockville) በሚገኝ የ MCPS የጤና ጥበቃ አገልግሎት ማእከል ሁሉም ክትባቶች ለቤተሰቦች በአነስተኛ ወጪ ይሰጣሉ። እባክዎን ልጅዎ የወሰዳቸውን ክትባቶች ማስረጃ በሚገባ ይያዙ።

በትምህርት አመት ውስጥ ልጅዎ የጥርስ፣ የመስማት፣ የማየት፣ የቁመት እና የክብደት ምርመራዎች/መለኪያዎች ይደረግለ(ላ)ታል።

ልጅዎ በትምህርት ቀናት በሃኪም የታዘዘ ወይም ያለ ሃኪም ትዕዛዝ ከመድሃኒት መሸጫ ቤት መደርደርያ ተገዝቶ  የሚወሰድ መድሃኒት የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ከሆነ ፈቃድ ባለው/ባላት የህክምና ባለሙያ መድሃኒት የታዘዘበትን እና MCPS ቅጽ 525-13 ተሞልቶ ለት/ቤት መሰጠት አለበትበሃኪም የታዘዘ መድሃኒት ለመስጠት ፈቃድ መስጫ ቅጽ በልጅዎ ት/ቤት እና በ MCPS ድረገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/525-13.pdf). በሐኪም የታዘዘ መድሃኒት በመድሃኒት ባለሙያ በተገቢዉ ምልክት ተደርጎበት በትክክለኛ የመያዣ እቃ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት አለበት። ያለሃኪም ትእዛዝ የሚወሰድ ከመድሃኒት መሸጫ ቤት መደርደሪያ ላይ የሚገዛ መድሃኒት በተመረተበት ኦርጅናል እቃ ላይ በትክክል የተከደነ እና የታሸገ መሆን አለበት። MCPS ቅጽ 525-14፣ አናፍለክሲስ (Anaphylaxis) ያለበት-ያለባት ተማሪ ድንገተኛ እርዳታ ፣ epinephrine auto-injectors ለመጠቀም ህጋዊ ፈቃድ ባለው/ባላት የህክምና ባለሙያ ተመራጭ የማዘዣ ቅጽ(www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/525-14.pdf)። ሁሉም ዓይነት መድኃኒት በወላጅ/በሞግዚት አማካይነት ለት/ቤት በእጅ መሰጠት አለበት። ልጅዎ የጤና ችግር፣ በተለይ አስቸኳይ እርምጃ የሚጠይቁ እንደ አስም፣ የስኳር በሽታ፣ የሚጥል በሽታ፣ ወይም የተባይ ንድፊያ ወይም የምግብ አለርጂ ካለው/ካላት እባክዎን ለርእሰመምህር እና ለት/ቤቱ ነርስ ያስታውቁ።

## ወላጅ፣ ቤተሰብ፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ

የሔድስታርት ፕሮግራም፥ እያንዳንዱ በፌደራል ደረጃ ብቁ የሆነ ቤተሰብ "የቤተሰብ እድገት እቅድ (FDP)" የተሰኘውን  የቤተሰብ አጋርነት ስምምነት ፈቃድ ከተሰጠው የቅድመ መዋእለ ህጻናት/ሔድስታርት ሥራ ባልደረባ ጋር እንዲጎለብት ይፈልጋል። "የቤተሰብ እድገት እቅድ (FDP)" ማለት የቤተሰብ ጥንካሬዎችን እና ፍላጎቶችን ለማዳበር እና ቤተሰቦች የግል ግቦቻቸውን ማሳካት እንዲችሉ የሚረዳ አሰራር ነው።

የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ሰራተኞች ከሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር አጋርነት በመፍጠር ሥራ፣ መኖሪያ ቤት፣ ምግብ፣ ልብስ፣ የቤተሰብ ሊተርሲ፣ የቤት ውስጥ ጠብና ረብሻን መከላከል፣ እና የአደንዛዥ እፅ መጠቀምን ማስወገድ ለመሳሰሉት የድጋፍ አገልግሎቶች ወላጆችን/ሞግዚቶችን  ከመገልገያዎች ጋር ያገናኛሉ። በቅድመ መዋእለ ሕጻናት/ሄድስታርት እና በማህበረሰብ ኤጀንሲዎች መካከል አገልግሎቶችን ለማቀናጀት እና የጥረቶችን ተደራራቢነት ለማስወገድ ስለሚጠቅም ቤተሰቦች FDP ሞልተው እንዲያጠናቅቁ ይበረታታሉ።

የማኅበረሰብ ሪሶርስ መረጃ እና ድጋፍ ለልጅዎ ክፍል በተመደበው/ችዉ የቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ በኩል ይሰጣል።  በ 240-740-4530 ያግኙዋቸዉ። እያንዳንዱ ቤተሰብ ወቅታዊ እና የወደፊቱን ፍላጎቶች ለማገዝ የማህበረሰብ ሪሶርስ መመሪያ ያገኛል። የድንገተኛ እና የተቃወሰ ችግር ጊዜ ጣልቃ ገብነትን ጨምሮ፣ ሁለቱም የግል እና የቤተሰብ ምክር (ካውንስሊንግ)፣ በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ማህበራዊ ሰራተኞች በኩል ይሰጣል። ሁሉም መረጃ በሚስጢር ይያዛል።

በየወሩ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ቤት ውስጥ የወላጅ/አሳዳጊ የትምህርት አውደጥናት ለማዘጋጀት/ለማቀድ የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛና የማስተማር ቡድንን እንዲረዱ ይጋበዛሉ። ርዕሶቹ የሚያካትቱት የሕፃን ዕድገትና መዳበር፣ ጤና እና የተመጣጠነ ምግብን፣ ለት/ቤት ተሳትፎ የወላጅ/የአሳዳጊ ዝግጁነትን፣ ቋንቋ እና ሊተርሲ እንዲሁም ስለ ግላዊ ደህንነት የመሳሰሉትን ነው። እንዲሁም፣ የወላጆችን ተሳትፎ እና በስብሰባ መካፈልን የበለጠ ለማመቻቸት የዙም ስብሰባዎች ይካሄዳሉ። የስብሰባ መለያ ኮድ እና የይለፍ ቃል የመሳሰሉት  የስብሰባ መረጃዎች በቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ በኩል በቅድሚያ ይገለጻሉ።

ከፍተኛ ጥራት ያለው የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ፕሮግራም በማግኘት ልጆችና ህጻናት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ለማስቻል ልጆች/ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሰራተኞች ችሎታቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውን እና ጉልበታቸውን ማካፈል አለባቸው በፕሮግራሙ ላይ የሚሳተፉ ወላጆች/አሳዳጊዎች መማር እና ማጋራት አስፈላጊ መሆኑን  ለልጆቻቸው ያሳያሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች በሚከተሉት መንገዶች ይሳተፋሉ፡-

ስለ ፕሮግራሙ ምንነትና እንቅስቃሴ አወሳሰን ላይ በሚከተሉት መንገዶች ማገዝ—

- በፖሊሲ ካውንስል ስብሰባዎች ላይ የመሀከል ተወካይ የሚሆን/የምትሆን አንድ ወላጅ /አሳዳጊ መምረጥ፣
- የመመርያ ምክር ቤት ስብሰባዎች መከታተል፣
- የማእከል ስብሰባዎች ማደራጀትና ማካሄድ፣
- ማዕከሉ እና መርሃግብሩ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲሰራ የማገዣ መንገዶችን ማቀድ፣
- በመርሃግብሩ በጀት እና በፕሮጀክት እቅድ ላይ መስራት፣ እና
- በአመታዊ ፕሮግራም ግምገማ ማገዝ።

በመማርያ ክፍል እንደ በጎ-ፈቃደኛ፣ ተመልካች፣ ወይም የሚከፈለው ሰራተኛ ሆኖ መስራት—

- የመማርያ ክፍል በመጎብኘት፣
- የመስክ ጉዞዎችን አጃቢ-ተቆጣጣሪ በመሆን፣
- በመማርያ ክፍል አዘውትሮ በጎ-ፈቃደኛ በመሆን፣
- እንደ ረዳት መምህር፣ ተለዋጭ ረዳት መምህር፣ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ፣ ወዘተ ሆኖ መቀጠር።

ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች የሚከተሉትን የሚያካትት እንቅስቃሴዎችን ማጎልበት፡-

- የቤተሰብ የተግባር እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ማካሄድ፣

- ከካውንቲና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ማህበረሰቦችን ለማሻሻል መስራት፣
- በማህበረሰብ መገልገያዎች መጠቀም፣

ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ሰራተኛ ጋር በመተባበር፣ የሚከተሉትን በማካተት ከልጆቻቸው ጋር ቤት ዉስጥ መሥራት፡-

- ልጆች እንዲማሩ የሚያበረታቱ ጨዋታዎችን ወይም እንቅስቃሴዎችን በቤት ውስጥ መጠቀም፣ እና
- ስለ ልጅ የአእምሮና አካላዊ መዳበር የተማሯቸውን ቴክኒኮች መጠቀም።

## በጎ-ፈቃደኞች

የወላጅ/ሞግዚት በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ተሳትፎ እጅግ በጣም አስፈላጊ እና የሚበረታታ ነው። ወላጆች/አሳዳጊዎች የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት/ሄድ ስታርት ልጆቻቸውን ክፍሎችን በማስጎብኘት ይረዷቸዋል። በተጨማሪም፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የመስክ ጉዞዎች በመሄድ፣ ፕሮግራሙን ለማሻሻል አስተያየቶችን በመስጠት፣ እና የክፍል ውስጥ ቁሳቁሶችን በቤት ውስጥ በማዘጋጀት ያግዛሉ። እንደ አንድ መደበኛ በጎ-ፈቃደኛ ሆነው ማገዝ ከፈለጉ፣ ከልጅዎ መምህር ጋር ይወያዩና ከሳምንት በየትኛው ቀን በመማርያ ክፍል በጎ-ፈቃደኛ ለመሆን እንደሚቻልዎት ፕሮግራም ያድርጉ። በቀን በቂ ሰአት ካላገኙ፣ ከቤት ሆነው ማገዝ ስለሚችሉባቸው ሌሎች መንገዶች ተወያዩ። ለተጨማሪ መረጃ ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ክፍል በ 240-740-4530 ይደዉሉ።

የበጎ ፈቃደኞች በሙሉበመደበኛነትትምህርት ቤቶችን እና ተማሪዎችን የምትደግፉ እና የመስክ ጉዞዎች ላይ የምትሳተፉ፣ በአውታረ-መረብ ላይ የሚሰጠውን "Recognizing and Reporting Child Abuse and Neglect." ስልጠና ማጠናቀቅ ይኖርባችኋል። ስልጠናዉ በእንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ቻይንኛ፣ ኮሪያኛ፣ ፖርቹጋልኛ፣ እና ቪዬትናምኛ በ MCPS ድረገጽ፣ www.montgomeryschoolsmd.org ላይ ይገኛል። ስልጠናውን ሲጨርሱ፣ የማጠናቀቂያውን የምስክር ወረቀት በማተም ለልጅዎ ትምህርት ቤት መስጠት አለብዎት። ሁሉም በጎ ፈቃደኞች በእያንዳንዱ የእንቅስቃሴ መጀመሪያ እና ማብቂያ የጎብኚ አስተዳደር ሲስተም (VMS) በመጠቀም፣ ት/ቤት ህንጻ ውስጥ ሲገቡ እና ሲወጡ መፈረም እና ሁልጊዜ የራስዎን የበጎ ፈቃደኛ መታወቂያ መለያ ስም ያለበትን መጠቀም እንዳለብዎት ያስታዉሱ።

ለመማርያ ክፍል በጎ-ፈቃደኛ ከመሆንዎ በፊት የሳምባ ነቀርሳ (TB) ምርመራ እንዲያደርጉ ይመከራሉ። የሣምባ ነቀርሳ (TB) ምርመራ ለማድረግ፣ እባክዎን ለልጅዎ ት/ቤት ነርስ ይደውሉ።

## መጓጓዣ/ትራንስፖርት

ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ወደ አውቶቡስ ማቆሚያ ለማድረስ፣ በአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ፣ እና ከአውቶቡስ ጣቢያ/ማቆሚያ ወደ ቤት ሲሄዱ ለልጆቻቸው ሃላፊነት አለባቸው። እባክዎ ጠዋት ጠዋት ልጅዎን ወደ አውቶቡስ ያድርሱ በየቀኑ ከሰአት በኋላ ልጅዎን ከአውቶቡስ ይቀበሉ። የአውቶቡስ መርሃግብሮች ግምታዊ ናቸው እናም በአየር ሁኔታ፣ በትራፊክ መጨናነቅ፣ እና በተማሪ ለውጦች ምክንያት ሊለያዩ ይችላሉ። ከመደበኛ መድረሻ ሰዓት ቢያንስ ከአምስት ደቂቃ በፊት በአውቶቡስ ማቆሚያ ላይ መገኘት በጣም ጥሩ ነው። አውቶቡሱን ማግኘት የማይችሉ ከሆነና ሌላ ሃላፊነት የሚሰማው አዋቂ እንዲተካዎ ከመረጡ (ለምሳሌ፣ የልጅ ተንከባካቢ፣ አያት) እባክዎ ለልጅዎ መምህር ወይም ለረዳት አስተማሪ በፅሁፍ ያስታውቁ። ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የትምህርት ቤት ስልክ ቁጥር በሞባይል ስልክዎ ወይም በሌላ ምቹ ቦታ ያስቀምጡ/ይያዙ።

እርስዎ ወይም የእርሶ ተወካይ በተመደበው ሠዓት ልጅዎን ለመረከብ ካልተገኙ፣ ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሳል/ትመለሳለች። እርስዎ ወይም ልጅዎን ለመረከብ የወከሉት ሰው ከአውቶቡሱ ልጅዎን ለመቀበል ሶስት ጊዜ ካልቻላችሁ፣ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ ጋር መገናኘት አለብዎት። ችግሮቹ ከቀጠሉ፣ የመጓጓዣ መብቶች ሊቋረጡ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የአውቶቡስ ላይ የባህሪ ችግሮች የአውቶቡስ መብቶችን ሊያቋርጡ ይችላሉ።

## የወላጅ/ማእከል ኮሚቴ ስብሰባዎች

ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የማስተማር ሰራተኞች፣ እና የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኞች መረጃ ሰጪ እና አዝናኝ የሆነ የወላጅ/አሳዳጊ ስብሰባ ለማቀድ ተባብረው ይሠራሉ።

በትምህርት ቤት እና/ወይም በዙም የወላጅ/አሳዳጊ ማእከል ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ የተጋበዙበት መልእክት በልጅዎ አማካይነት እቤት ይላክልዎታል። ቦታ ካለ ከልጅዎ ጋር አብረው በአውቶቡስ መሳፈር ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ፣ የሕጻናት እንክብካቤ ይሰጣል።

እያንዳንዱ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ክፍል ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚገኙበት አንድ የማዕከል ኮሚቴ አላቸው። የማእከል ኮሚቴው በሚከተሉት ምክንያቶች በትምህርት ሰአት በየወሩ ይሰበሰባል፡-

- ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲተዋወቁ ማገዝ፣
- ስለ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ክፍል የበጎ ፈቃደኞች እና የመስክ ጉብኝቶች ውሳኔዎችን መስጠት፣ እና ለተማሪዎች በጣም የተሻለውን ፕሮግራም በማቀድ መርዳት፣
- በትምህርት ቤትና በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ፕሮግራም መካከል የሁለትዮሽ ግንኙነት ማድረግ፣
- ከፖሊሲ ካውንስል እና ወደ ፖሊሲ ካውንስል የሚቀርቡ ቅሬታዎችና መርጃዎችን መላክ/መቀበል፣
- የማእከል ስራዎችን ማካሄድ እና በሚከተሉት ላይ መረጃ መጋራት -
  - » ልጆች እንዴት እንደሚያድጉና በአካልና በአእምሮ እንደሚዳብሩ
  - » ልጆች እንዲማሩ ለመርዳት አዝናኝ መንገዶች
  - » አልሚ ምግቦችን ለማዘጋጀት የምግብ ዶላሮችን ማብቃቃት
  - » እደጥበባትና ክህሎቶች
  - » ልጆችን መኖርያ ቤት ውስጥ እንዲማሩ ማገዝ

ቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት የቤተሰብ ፕሮግራም ነዉ። የእርስዎን እርዳታ በመማርያ ክፍል፣ በፖሊሲ ካውንስል፣ እና በሙሉው ፕሮግራም እንፈልገዋለን።

# ሌላ መረጃ

## ቀዳሚ ሄድስታርት/Early Head Start

ቀዳሚ ሄድስታርት/Early Head Start እድሜአቸው ከወሊድ እስከ 3 አመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች አስደናቂ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ ከሄድስታርት/Head Start ጋር ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ አገልግሎቶች እና የተወሰኑ ልዩ የሆኑትን ለቀዳሚ ሄድስታርት/Early Head Start ያቀርባል። ለማመልከት፣ ቤተሰቦች እርጉዝ ወይም እድሜአቸው 26 ወሮች ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው መሆን አለባቸው።

ስለ ፕሮግራሙ ተጨማሪ መረጃ የሚያገኙበት እነሆ:-
በጌተርስበርግ/Gaithersburg እና በአፕካዉንቲ/Upcounty አካባቢዎች:-
Family Services, Inc., ሼፐፓርድ ፕራት አካል ወደሆነው ቀዳሚ ሄድ ስታርት 301-840-3272 ይደውሉ።

በሲልቨር ስፕሪንግ እና ሮክቪል አካባቢዎች:- The Reginald S. Lourie Center, Early Head Start at 301-891-1900 ይደዉሉ።

በላንግሊ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ አካባቢ:- CentroNía, Early Head Start 301-543-8040 ይደዉሉ።

## የህፃናት እንክብካቤ

የልጅ እንክብካቤ ሰጪ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ LOCATE መደወል ይችላሉ፡- የሕፃናት እንክብካቤ በስልክ ቁጥር 1-877-261-0060፣ ወይም ቻይልድሊንክ (ChildLink) 240-777-4769 በነፃ እርዳታ ፈቃድ ያለው የሕጻናት ተንከባካቢ፣ የትምህርት እድሜ ፕሮግራም፣ የሰመር ካምፕ፣ ቅድመ ትምህርት፣ እና/ወይም የመሰናዶ ት/ቤት ፕሮግራም ለማግኘት። LOCATE፣ የእንክብካቤ ሰዓቶችን፣ ቦታ፣ የልጆች ብዛትና እድሜ፣ እና የልጅ እንክብካቤ ክፍያ በመሳሰሉ፣ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት አገልግሎት ሰጪዎችን ለይቶ ይገልጻል። ይህን አገልግሎት በበርካታ ቋንቋዎች ማግኘት ይቻላል።

LOCATE በትምህርት ቤቱ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ወይም አጠገብ የሚገኙትን አቅራቢዎች ለይቶ ማወቅ ይችላል። በተጨማሪ፣ ካውንስለሮች መልካም ፕሮግራሞችን ስለ መለየት ጥቆማዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ትክክለኛ ፕሮግራም ለልጃቸው እንዲመርጡ ለማገዝ ለክትትል ቀላል የሆኑ ጥቆማዎችን ይሰጣሉ። ማፈላለግ/LOCATE፡- "Child Care" በሜሪላንድ የትምህርት ዲፓርትመንት የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ሰጪዎችንና የልጆች እንክብካቤ ማእከሎችን (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት የልጆች እንክብካቤ ጽ/ቤት) ተቀባይነት ያላቸውን ሁለቱንም ለይቶ ያሣያል።

ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ባህርዮች የሚያንፀባርቁ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ፕሮግራሞች ማግኘት አለባቸው፡- ሰራተኛው/ዋ የልጆቹን እድገታዊ ፍላጎቶች የሚገነዘብ-የምትገነዘብ፤ ፕሮግራሙ የተለያዩ ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ያሉት፣ አቅርቦቶች፣ እና ከተገልጋዮች እድሜ ጋር አግባብ የሆኑ መጫወቻዎች ያሏቸው፤ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች መልካም አቀባበል ያላቸውና የሚያሳትፉ፤ መርሃግብሮችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና ፕሮግራሞችን በሚመለከት ሰራተኛው(ዋ) ከት/ቤት ባልደረቦች ጋር በትብብር አብረው የሚሠሩ።

በስቴት እና የካውንቲ ህጎች ድንጋጌ መሠረት ከ8 አመት በታች የሆኑ ልጆች ሁልጊዜ በወላጅ/አሳዳጊ፣ የልጅ ተንከባካቢ፣ ወይም ቢያንስ 13 አመት እድሜ ባለው/ባላት ልጅ ቁጥጥር እንዲጠበቁ ይደነግጋሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጅ እንክብካቤ መረጃዎችን በዚህ ኦንላይን www.marylandfamilynetwork.org መፈለግ ይችላሉ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ/Montgomery County ጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች በኩል ለህጻን እንክብካቤ ለመክፈል የገንዘብ እርዳታ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ:- የሠራተኛ ቤተሰብ ድጋፍ (WPA) 240-777-1177 ይደዉሉ። ቅጂው እርስዎ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እንዴት እንደሚቻል ጨምሮ አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል። የሜሪላንድ ስቴት የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ለልጆች እንክብካቤ ክፍያ ብቁ ለሆኑ ሰራተኛ ቤተሰቦች ድጋፍ ያደርጋል፤ ወደ 1-877-227-0125 ይደውሉ።

## ቅድመ መዋዕለ ህፃናት የሙከራ ፕሮግራም (Pre-K+)

ይህ ሙሉ ቀን የሚካሄድ የ Pre-K ፕሮግራም ገንዘብ የሚገኘው ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት "Maryland State Department of Education (MSDE)" ነው። ፕሮግራሙ በ17 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 480 የአራት አመት እና 20 የሶስት አመት ተማሪዎችን ያገለግላል፡- ቤል ፕሬ (Bel Pre)፣ ክሎፐር ሚል (Clopper Mill)፣ ፌርላንድ (Fairland)፣ ከምፕ ሚል (Kemp Mill) ጆአን ለለክ አት ብሮድ ኤከርስ (JoAnn Leleck at Broad Acres)፣ መክአሉፍ (McAuliffe)፣ ሚል ክሪክ ታወን (Mill Creek Towne)፣ ሞንትጎመሪ ኖልስ (Montgomery Knolls)፣ ሮሊንግ ተሬስ (Rolling Terrace)፣ ታኮማ ፓርክ (Takoma Park)፣ ሃሪት ቱብማን (Harriet Tubman)፣ ሱሚት ሆል (Summit Hall)፣ ቬርስ ሚል (Veirs Mill)፣ ዋሽንግተን ግሮቭ (Washington Grove)፣ ዌለር ሮድ (Weller Road)፣ ዊተን ውድስ (Wheaton Woods) እና አፕካውንቲ የህጻናት ማእከል በዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Upcounty Early Childhood Center at Watkins Mill High School) መጓጓዣ እና ምሳ ይሰጣል። የቤተሰብ ገቢ የድህነት ጠለል ደረጃ 300 ወይም ከዚያ በታች መሆን አለበት። ቤተሰቦች በሄድስታርት ተሳትፎ ተመሳሳይ የድጋፍ አገልግሎቶች እና እድሎችን ያገኛሉ።

# ብዙ ጊዜ በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ቃላት

**ACYF**
ለልጆች፣ ወጣቶች፣ እና ቤተሰቦች አስተዳደር—የሄድስታርት ፕሮግራምን የሚቆጣጠር የፌደራል ኤጀንሲ።

**የህብረተሰብ ተወካይ**
ከፖሊሲ ምክር ቤት ጋር የሚያገለግል-የምታገለግል፣ ነገር ግን የአሁን ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድስታርት ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ያልሆነ/ች፤ በአብዛኛው ቀደም ብለው በፕሮግራሙ ውስጥ ልጆች የነበሯቸዉ ወይም የአንድ ድርጅት ተወካይ ወይም የካውንቲ ወኪል የሆነ/ች።

**ስርአተትምህርት**
የልጆችን ትምህርት የሚደግፍ የማስተማር መዋቅር።

**የቤተሰብ ልማት ዕቅድ (FDP)**
የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞቸው ድጋፍ ተጨምሮበት፣ የቤተሰብ ግቦችን ለማስቀመጥና ለክትትልና ለአፈፃፀም እርምጃዎች የሚረዱ የፅሁፍ እቅድ ለማዳበር፣ የቤተሰቦች እድል።

**የገንዘብ እርዳታ/Grant/**
በቀረበው የፅሁፍ ሀሳብ እንደተገለፀው፣ የ ሄድስታርትን ፕሮግራም ለማንቀሳቀስ የሚሰጥ ገንዘብ።

**እርዳታ ተቀባይ ኤጀንሲ**
የሄድስታርትን ፕሮግራም ለማንቀሳቀስ ከ ACYF የሚሰጠውን ገንዘብ የሚቀበል ኤጀንሲ—የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ ድርጊት ኤጀንሲ - Montgomery County Community Action Agency።

**ተወካይ ኤጀንሲ**
ለቅድመ መዋለ ሕጻናት/ሄድስታርት ፕሮግራም የዕለት ተዕለት ስራ ሀላፊነት ያለበት ኤጀንሲ—የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)።

**የፖሊሲ ካውንስል**
ለቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ፕሮግራሞች ፖሊሲን በማዘጋጀት የሚረዱ የወላጅ-ማዕከል ኮሚቴ ተወካዮች።

**የፌዴራል ግምገማ**
በፌደራል መንግስት በየሶስት አመት የሚከናወን የቅድመ-ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ፕሮግራም ግምገማ።

**ለትምህርት ቤት ዝግጁነት**
አንድ ልጅ - አንዲት ለት/ቤት ስኬታማነት የሚያስፈልጉ ክሂሎቶች፣ ችሎታዎች፣ እና ዝንባሌዎች አሉት-አሏት።

**ራስን መገምገም**
የፕሮግራም ራስን የመገምገም ሂደት በወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች በየዓመቱ ይካሄዳል።

---

## የቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት TOT መስመር :-

## 240-740-4580

**ስለ ልጃቸው ባህሪ ወይም እድገት ጥያቄ ወይም አሳሳቢ ጉዳይ ሲኖርባቸው ለቅድመ መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲጠቀሙ ልዩ የስልክ መስመር አለ። የፕሮብለሞች አያያዝ ላይ ልዩ አስተያየቶች/ሃሳቦች ሲያስፈልጉ ይደውሉ። የ TOT መስመር ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 8፡ 30 a.m. እስከ 5:00 p.m. ይሠራል።**

---

# የ 2022 ካላንደር

| | |
|---|---|
| ኦገስት 22-26 | የመምህራን የባለሙያ ቀን |
| ኦገስት 29 | የተማሪዎች የት/ቤት መጀመሪያ ቀን (K-12) |
| ኦገስት 29-ሴፕቴምበር. 2 | ሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት የሙከራ (Pre-K+) የቤት ጉብኝት |
| ሰፕተምበር 5 | የወዛደር ቀን—ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸዉ |
| ሴፕቴምበር 6 እና 7 | በቅደምተከተል የሚከፈቱ Head Start፣ Pre-K፣ እና Pre-K Pilot (Pre-K+) ተማሪዎች |
| ሴፕቴምበር 8 | ለሄድስታርት፣ ቅድመ መዋዕለ ህፃናት፣ እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) ለሁሉም ተማሪዎች የመጀመሪያ ቀን |
| ሴፕቴምበር 14 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ሰፕተምበር 26 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ሴፕቴምበር 30 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ኦክተበር 5 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኦክቶበር 6 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኦክቶበር 8 | የሄድስታርት ለወላጅ የሚሰጡ መግለጫዎች ይጠናቀቃል |
| ኦክቶበር 12 | የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) አስተማሪዎች ስልጠና—የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም |
| ኦክተበር 19 | የቅድመ መዋዕለ ህፃናት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ህፃናት ተማሪዎች ትምህርት የለም |
| ኦክቶበር 20 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኦክቶበር 24 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኦክተበር 31 | የቅድመሙዓለህፃናት/Prekindergarten መግለጫ ይጠናቀቃል |
| ኖቬምበር 3 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኖቬምበር 7 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም፥ የሩብ አመት እቅድ መጨረሻ |
| ኖቬምበር 8 | የምርጫ ቀን — ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸዉ |
| ኖቬምበር 9 | የአባትነት ተግባር–6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኖቨምበር 16 | የልጅ እድገት እና እድገት የወላጅ ስብሰባ --6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኖቨምበር 17 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኖቬምበር 21 እና 22 | የወላጅ - መምህር ኮንፈረንሶች— ለ Pre-K፣ Pre-K+ እና ሄድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም |
| ህዳር 23፣24 እና 25 | Thanksgiving—ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ |
| ዲሰምበር 1 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ዲሰምበር 7 | የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) አስተማሪዎች ስልጠና —የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) ተማሪዎች ትምህርት አይኖራቸውም |
| ዲሰምበር 7 | ቋንቋ እና ማንበብና መጻፍ የወላጅ ስብሰባ—6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ዲሴምበር 9 | የዊንተር ብርሃን ክውነት |
| ታህሳስ 12-15 | ብሄራዊ መሪ ጅምር የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ - Dallas, TX |
| ዲሰምበር 14 | የቅድመ መዋዕለ ህፃናት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ህፃናት ተማሪዎች ትምህርት የለም |
| ዲሴምበር 15 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ዲሴምበር 16 | የዊንተር ብርሃን ክውነት |
| ዲሰምበር 23–31 | የዊንተር ዕረፍት—ለተማሪዎች እና ለአስተማሪዎች ምንም ትምህርት ቤት የለም፤ ቢሮዎች ዲሴምበር 26 እና ጃንዋሪ 2 ዝግ ይሆናሉ |

# የ 2023 ካላንደር

| | |
|---|---|
| ጃኑዋሪ 2 | የዊንተር ዕረፍት - ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ። |
| ጃንዋሪ 3 | ክፍል ይጀመራል |
| ጃንዋሪ 5 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ጃንዋሪ 11 | የአባትነት ተግባር–6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ጃኑዋሪ 16 | የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ጁኒየር ቀን - ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ። |
| ጃኑዋሪ 19 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ጃንዩወሪ 27 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም፥ የሩብ አመት እቅድ መጨረሻ |
| ፌብሩዋሪ 2 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ፌብሩዋሪ 15 | የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) አስተማሪዎች ስልጠና—የሄድስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ (Pre-K+) ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም |
| ፌብሩዋሪ 16 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ፌብሩወሪ 20 | የፕሬዝዳንቶች ቀን - ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው። |
| ፌብሩወሪ 21-24 | ሄድ ስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ(Pre-K+) የቤት ጉብኝት—ለሄድ ስታርት እና ቅድመ መዋዕለ ህፃናት ሙከራ(Pre-K+) ትምህርት የለም |
| ፌብሩዋሪ 22 | የቅድመ መዋዕለ ህፃናት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ህፃናት ተማሪዎች ትምህርት የለም |
| ማርች 2 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ማርች 3 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ማርች 8 | የአባትነት ተግባር–6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ማርች 15 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ማርች 16 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ማርች 22 | ጤና እና የተመጣጠነ ምግብ የወላጅ ስብሰባ --6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ማርች 31 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኤፕሪል 3-10 | የስፕሪንግ እረፍት—ለተማሪዎች እና ለመምህራን ት/ቤት አይኖርም፣ ጽ/ቤቶች ኤፕሪል 7 እና 10 ዝግ ይሆናሉ። |
| ኤፕረል 6 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ኤፕረል 19 | ስለ ግል ደህንነት የወላጅ ስብሰባ -- 6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ኤፕረል 20 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ኤፕረል 21 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ሜይ 4 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ሜይ 8–11 | ብሔራዊ ሔድ ስታርት ኮንፈረንስ–ፎኒክስ (Phoenix)፣ AZ |
| ሜይ 10 | የአባትነት ተግባር–6፡30 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም |
| ሜይ 18 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ሜይ 29 | ሜሞሪያል ቀን—ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ |
| ጁን 1 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም— ቨርቹወል/ዙም |
| ጁን 8 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ–6፡00 ፒኤም—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ጁን 15 | ለሁሉም ቅድመ-ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ተማሪዎች የመጨረሻ የትምህርት ቀን |
| ጁን 19 | Juneteenth በዓል - ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ይሆናሉ። |
| ጁን 20 | የባለሙያ ቀን ለመምህራን |

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ህትመት፦Department of Materials Management for the Division of Early Childhood and Title I Programs, and Recovery Funds

ስልክ፦ 240-740-4530 TTY ፦ 301-230-5462

0039.23ct • Editorial፣ Graphics & Publishing Services • 8/22 • 200